# የኮርስ የቤት ስራ አሰጣጥ ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ደንቦች

የትምህርት ሂደቱ ዋናው ማእከል ተማሪው ነው። በመሆኑም ተማሪዎች በራሳቸው ሂደት ኋላፊነት መውሰድ እንዳለባቸው ይጠበቃል። እነርሱ ከአስተማሪዎችና ከጎደኞቻቸው ጋር በመተባበር ይሰራሉ እንዲሁም ከክፍል ውስጥ ስራዎችን እና ውይይቶች አስተዋፆ ያደርጋሉ። የተሰጣቸውን ስራዎች በሙሉ አስተማሪው በሚያዘው መሰረት፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ እና የመመዘኛ መስፈርት መሰረት ያጠናቅቃሉ። በተጨማሪም ስራቸውን ይከልሳሉ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተሰጠው ደረጃ እና የሚጠበቀው ውጤት ያልተገኘ ከሆነ። የዚህ ሂደት አካል የራሳቸውን እድገት ለውጥ በመከታተል በየጊዜው የሚሰጡ የፈተና ውጤቶችና የመጨረሻውን ውጤት ጭምር በመከታተል ተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ ያደርጋሉ አጠቃላይ የሚፈልገውን የመመዘኛ ደረጃ ላይ ለመድረስ በግል የሚታየውን የእድገት ለውጥ ለመረዳት።

የሚሰጣቸውን መረጃ ዝም ብለው ተቀባይ ከሚሆኑ ይልቅ ተማሪዎች ትርጉም እንዲኖረው ራሳቸው እንዲረዱ በማድረግ የሚያጠኑት ትምህርት ምንነት - የትምህርት ይዘቱን በሚገባ መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የጠለቀ ይዘት ያለውን ጥያቄዎችን በመጠይቅ ጭምር እንዲረዱ ማድረግ ። በተቻለ መጠን ተማሪዎች ስለሚማሩት ርእስ የመተንተን እና የጠለቀ አመለካከት እንዲኖራቸው ይታሰባል። በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ብቃትና ኋላፊነት ማሳየት፣ በራሳቸው የትምህርት ሂደት በተከታታይ ንቁ እና ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዳላቸው ያረጋግጣሉ። በዚህ ቁርጠኝነት መሰረት ተማሪዎች ሲመረቁ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የኮሌጅ ዝግጁነት አምስት ተፈላጊ ችሎታ መስኮች ፤ የተወሳሰበ ይዘት ያለው ንባብ መረዳት፣ በሚመሩት የትምህርት ይዘት ፅሑፍ ማዘጋጀት፣ በሚከታተሉት የትምህርት መስክ ትንተና ፣ የመረጃ ትንተና ትርጉም እና ውጤታማ የሆነ የንግግር እና የማዳመጥ ችሎታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል።

## የኮርስ የቤት ስራ የአሰራር ትርጎሜ

በተማሪዎች የሚሰራ ማንኛውም የቤት ስራ ከትምህርቱ ይዘት ጋር በተያያዘ ያላቸውን እውቀት እና ክህሎታቸውን ማሳደግ።

የቤት ስራ፣ የንባብ የቤት ስራ ጭምሮ አንድ ቁም ነገር ሊኖረው ይገባል እንዲሁም ኮርሱ ከሚፈለገው ክህሎት እውቀትና ከኮርስ ደረጃ ጋር የተጣመረ መሆን አለበት ። በተለይም የኮርስ ስራ በፖሊሲው IFA( የምዘና እና ግምገማ) እና ደንቦች ላይ በተቀመጠው መሰረት የተማሪውን እድገት በመመዘን ማገልገል ይኖርበታል። ምዘና እና ግምገማ እና ተያያዥ ደንቦች፤

## የኮርስ የቤት ስራ አላማዎች ፤

- ተማሪው በክፍል ውስጥ የሚያገኘውን አጠቃላይ እውቀትና ክህሎቶች ራሱን ችሎ በተግባር ማዋል መጠናከርና ማሻሻል፣
- ተማሪው በክፍል ውስጥ የሚማረውን እውቀት ግንዛቤ እና ለምን እንደሚማሩ ጥልቅ ግንዛቤ መፍጠር፣

- የተማሪውን በረዥም ጊዜ የታቀዱ ግቦችን ለማሳከት በሚደረግ ሂደት ራስን የመምራትና አቅጣጫ ማስተካከል የተመረጡ የትምህርት አላማዋች ለማሳካት የተማሪውን የሃላፊነት ማሳደግ ፣
- ተማሪዋች ራሳቸውን ችለው እየጨመረ በሚሄድ ራስ መምራት እውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በስራ የሚያውሉበት እድል መስጠት፣
- አስተማሪን ማእከል ካደረገ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ወደ አቅጣጫ የማመልከት እና በራስ ጥረት እውቀት የማግኘት ሞዴል የመሸጋገር እድል መስጠት፣

**የኮርስ የቤት ስራ አሰጣጥ የአስተማሪ መመሪያዋች፤**

የኮርስ የቤት ስራ አሰራር ትርጉም ያለው የተማሪው የማስተማር ፕሮግራም ቀጣይ ሂደት መሆን አለበት። እንዲሁም ግልፅ እና ከሚጠናው የትምህርት ርእስ ጋር ትርጉም ያለው ትስስር መኖር አለበት።

ሁሉም የኮርስ የቤት ስራ በግልፅ የተቀመጠ አላማ እና ከታች ከተገለፁት ቢያንስ ከአንዱ ጋር ወይም ከዚያ በላይ ካሉት ጉዳዮች ጋር አብሮ የሚሄድ መሄድ አለበት።

- ለተማሪዋች የራሳቸው ጊዜ እንዲኖራቸው መስጠት ለመለማመድ እና በክፍል ውስጥ የተማሩትን እንዲለማመዱ።
- አዲስ እውቀት ለመማር እንደመነሻ እንዲሆን ቀደም ሲል የነበረውን እውቀት መከለስ ።
- ከዚህ ቀደም ያልተማሩትን አዲስ የትምህርት ይዘት መረዳት እንዲችሉ ተማሪዋች አዲስ መረጃ እንዲያገኙ ማዘጋጀት።
- በክፍል ውስጥ የሰሙትን መረጃ ለማብራራት ነገር ግን ጠለቅ ያለ ግንዛቤና እና በተማሪዋች በራሳቸው እንዲጠቀሙበት ማድረግ።
- የትምህርቱን ይዘት ለመረዳት የተሰጣቸውን የንባብ ስራ እንዲያጠናቅቁ ለተማሪዋች ጊዜ መስጠት።
- የትምህርቱ ይዘት ዋነኛ አካል በራስ የሚካሄድ የተማሪዋችን የጥናትና ምርምር እንዲረዱ ማበረታት።
- የኮርስ መጠናቀቂያ(የስሚቲቭ) ) ፈተናዋችን (ለምሣሌ ፈተና፣ የተሰጡ ፕሮጀክት ስራዋችን) ሊኖር የሚችለው በማገናዘብ ለተማሪዋች የኢጋማሽ ሴሚስተርና በየምእራፍ የሚሰጡ መመዘኛ(ፎርማቲቭ) ፈተና ምላሺ መስጠት።

የኮርስ የቤት ስራ የተመረጠ እና ግልፅ የሆነ አቅጣጫ ምን ውጤት እንዲሚገኝ እና ሊፈፀሙ የሚገባቸውን <u>S.M.A.R.T.</u> ግቦች (የተመረጡ፣ የሚለኩ፣ ሊሳኩ የሚችሉ፣ ከእውነታው ጋር የተዛመዱ እና በጊዜ ገደብ የሚፈፀሙ (ታይም ሴንሲቲቭ) የሆኑ የሚያካትቱ መሆን አለባቸው።

የኮርስ የቤት ስራ የተለያየ መሆን ይገባዋል እንደ ተማሪዋቹ ፍላጎት የሚለያይ እና የሚቻል ከሆነ ልዮነት በተማሪው ሁኔታ፣ የመጀመሪያ ቋንቋ፣ የማጠናከሪያ ድጋፍ እና /ወይም የተግባር አፈፃፀም እና የቤተሰብ ድጋፍ ሲስተም መሰረት ሊለያይ ይችላል።

በአስተማሪ የትብብር እቅድ ዝግጅት እድሎች መገኘት ላይ በመመስረት አስተማሪዋች ለሚከተሉት ጉዳዮች የተለየ አትኮሮት እንዲሰጡ ይበረታታሉ።

የኮርስ የቤት ስራ ፖሊሲ ደንቦች በሚጠየቀው አሰራር ተከትሎ የማከናወን አስፈላጊነት፤

- በግድ መወሰድ ያላባቸው የኮርስ ስራዋች በረዝም የእረፍት ጊዜ አይሰጡም።(ለምሳሌ፣ ታንክስ ጊቪንግ (Thanksgiving) ፣ የክረምት እና ስፐሪንግ እረፍት ወቅት፣ ወዘተ...) በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ የእረፍት ጊዜ መውጫው ቀደም ብሎ ያሉትን የሁለት ዝግ (የቤት ስራ የማይሰጥባቸው) ቀናት ጭምር።

- የረዝም ጊዜ የሚጠይቁ የቤት ስራዎች መመለስ ያለባቸው ተማሪዋቹ እና ሰራተኞቹ ከረዝም እረፍት ከተመለሱ በኋላ ባሉት ጊዚያት ቢያንስ በአምስት ቀናት ጊዜ ውስጥ መሆን የለበትም።
- ከትምህርት እረፍት የሚወሰድበት ጊዜ በይፋ የሚጀመርበት ጊዜ እረፍት ከመጀመሩ በፊት ካለው የመጨረሻ የትምህርት ቀን ጀምሮ እስከ ከእረፍት መልስ ትምህርት እስከሚጀመርበት ቀን ድረስ ይቆያል።
- የቤት ስራ ብዛት "የትራፊክ ጭንቅንቅ" እንዳይፈጠር በርካታ ትላልቅ የረዝም ጊዜ የቤት ስራዎች (ለምሳሌ፣ ፅሁፎች፣ የምርምር ፕሮጀክቶች፣ የአንድ ምእራፍ ፈተና ፣ ወዘተ..) በአንድ ወቅት የማቅረቢያ ጊዜ እንዳይሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ለእያንዳንዱ የረዝም ጊዜ የሚጠይቅ የቤት ስራ ለማጠናቀቅ ቢያንስ አንድ ሙሉ ሳምንት መሰጠት ይኖርበታል። በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከአንድ በላይ የረዝም ጊዜ የሚጠይቅ የቤት ስራ መስጠት ከመጠን በላይ እንደሆነ ይቆጠራል።

የማጠናቀቂያ ጊዜ እና ለዋና ፕሮጀክቶች የሚጠየቁ ስራዎች(ለምሳሌ፣ ፅሁፎች፣ የምርምር ፕሮጀክቶች፣ የአንድ ምእራፍ ፈተና ፣ወይም ማንኛውም ከፈተና ውጤት ነጥብ ጋር እኩል የሆነ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ) በአንደኛ ደረጃ ካለው የድጋፍ ሰጪ /ሪሶዋርስ አስተማሪ ፣በመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ካሉ የተባባሪ የእቅድ ዝግጅት ቡድን አባለት ጋር እና በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ደረጃ ካሉ የትምህርት አሰጣጥ ቡድኖች ጋር (ለምሳሌ ዲፖርትሜንት እና የክፍል ደረጃ የትምህርት ይዘት ቡድን፣ የዓለም አቀፍ አካዳሚ ወዘተ..) በቅንጅት መፈፀም ይኖርበታል።

የኮርስ የቤት ስራ ከመስጠት በተጨማሪ አስተማሪዋች ከተማሪዋች ጋር መስራት አለባቸው በራሳቸው የመመራት እና የአደረጃጀት ክህሎቶችን የመቆጣጠር እና ራስን የመምራት አተገባበር ለማጠናከር ዘዴዋችን በመጠቀም ለምሳሌ ፤ የጊዜ ሰሌዳ የማቀናጀት እና የቅደም ተከተል (ስኬጅውሊንግ) አወጣጥ በመጠቀም ፣ ሳምንታዊ የኮርስ የቤት ስራ ፋይል ምርመራ በማድረግ፣ የኮርስ የቤት ስራ አፈፃጸም ራስን የመገምገም አሰራር በስራ በማዋል።

አስተማሪዋች ተማሪው ያልጨረሰውን የቤት ስራ እንዲያጠናቅቅ በማድረግ ወይም ተማሪው ባልነበረበት ጊዜ ያመለጠውን ለመሸፈን ሌላ የማካካሻ ስራ መስራቱን በማረጋገጥ ከተማሪዋችና ከወላጆች ጋር አብረው ይሰራሉ።

በመካከለኛ ደረጃ እና ከፍተኛ ሁለተኛ ት/ቤት ያሉ አስተማሪዋች ሁሉንም የኮርስ የቤት ስራዋች በብላክ ቦርድ የቤት ስራዋች በሚለው ገፅ ላይ በወቅቱ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ ይህም ፤ የቤትስራው በተሰጠበት እለት ወይም ስራው ከመሰጠቱ በፊት ይሆናል።

## የኮርስ የቤት ስራ መቆጣጠርና የመመዘን የአስተማሪዋች መመሪያዋች፤

ተማሪዋች የሚሰሮቸውን የኮርስ የቤት ስራዋች አስተማሪዋች ወቅታዊ መልስ አስተያየት መስጠት አለባቸው። (የፅሁፍ እና የቃል አስተያየት ድብልቅ በተጣመረ መልኩ፣ በተናጠል፣ በትንሽ ቁጥር ስብስብ ወይም የሁሉም ስብሰብ ባለበት ሁኔታ) ። ይህ አስተያየት የተማሪውን የትምህርት አቀባባል ሁኔታ ያጠናከራል።

በአንደኛ ደረጃ የቤት ስራ ማጠናቀቅ የትምህርት ዓይነት አቀባበል በሪፖርት ካርድ ላይ መገለፅ ይኖርበታል።

በሁለተኛ ደረጃ የቤት ስራ እንደመቅጫ ማገልገል አይኖርበትም። የኮርስ ነጥብ ተማሪው በተፈለገው የትምህርት ዓይነት የእውቀት ደረጃ ያለው መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል።

ተማሪው የተሰጠውን የኮርስ የቤት ስራ ማጠናቀቅ ወይም መጀመር የማይችልበት ሁኔታ ከታየ አስተማሪዋች ከወላጆች ጋር በተከታታይ ግንኙነት ያደርጋሉ። ተማሪው የተሰጠውን የኮርስ የቤት ስራ እንዲያጠናቅቅ ስትራቴጂዋች እንዲዘጋጁ ይደረጋል።

**የኮርስ የቤት ስራ አሰራር የአስተማሪ መመሪያዋች፤**

በክፍል ደረጃ እና /ወይም በቡድን እና በዲፖርትሜንት ከሚጠበቀው ስራ ጋር  የሚሄድ መሆኑን ለማረጋገጥ ትምህርት ቤቶች ከተሰጠው የቤት ስራ ጋር የሚጣጣም የተለመደ አሰራር ያዘጋጃሉ።

ከኮርስ የቤት ስራ የሚጠበቀው ነገር ለወላጆች እና አሳዳጊዋች በዓመቱ መጀመሪያ በስብሰባ ፣ ወደ ትምህርት ቤት የመመለሻ የምሽት ፕሮግራም ፣ በትምህርት ቤት ድረገፅ እና በደብዳቤ አማክኝነት ይገለፃል።

ትምህርት ቤቶች ለወላጆችና ለአሳዳጊዋች ልጆቻቸውን እንዴት ሊያግዙ እንደሚችሉ ውጤታማ የሆነ የአጠናን ስትራቴጂ እንዲያዳብሩ እና የኮርስ የቤት ስራ እንዲያጠናቅቁ የሚረዳ የስትራቴጂዋች ሃሳብ ያቀርባል የሚከተሉትን ዓይነት፤

- የቤት ስራውን ለመስራት ቦታ ማዘጋጀት እንዲሁም ጥናት ለማድረግ የተወሰነ ጊዜ ይሰጣል።
- ተማሪዋች ራሳቸውን ችለው እንዲያነቡ መፅሀፍ እና ሌሎች አመቺ ሁኔታዋችን ይፈጥራል።
- ለልጁ ማንበብ እንዲሁም ከልጅ ጋር አብሮ ማንበብ።
- ሁኔታ አመቺ ከሆነ ከቤተሰብ ጋር የመስክ ጉብኝት በማድረግ፣ የቤተመፅሀፍትና ሙዚየም በመጎብኘት ፣ በኢንተርኔንት በመፈለግ፣ ወዘተ.. የትምህርት ይዘቱን የማጠናከር ስራ መስራት።
- ከአስተማሪው ተጨማሪ ገለፃ የሚፈልጉ ጥያቄዋችን በማስታወሻ እንዲይዙ ተማሪዋችን እንዲበረታቱ ማድረግ።
- ከአስተማሪውና ከአማካሪዋች ጋር ቀጣይ ግንኙነት እንዲኖር ማድግ ።